**የምን አትርሱን ነው?** (ለመንግሥቱና ወግደረስ)

ከጌትነት

ስታሥሩ፣ ስትደፍሩ፣ ስትገድሉ ኖራችሁ፣
ውስጥ'ግር አንፍራችሁ፣ ፍሬ ቀጥቅጣችሁ፣
የልጅ ብልት በግፍ፣ እየመተራችሁ፣
ለወላጅ እናቱ፣ በግድ አብልታችሁ፣
አውሬነታችሁን፣ እንደማናውቃችሁ?!

ሕፃን አዛውንቱን፣ ለስቃይ ዳርጋችሁ፣
ዓይን ጎልጉላችሁ፣ ጥፍር ነቃቅላችሁ፣
ብረት አግላችሁ፣ በሴት ላይ ዶላችሁ፣
እህት እናቶችን፣ አሣር አሳይታችሁ፣
በግፍ ድርጊታችሁ፣ እንዳልቆሸሻችሁ?!
ዛሬም ባደባባይ፣ እንታይ አላችሁ?!

ዜጎች በቁም ተልተው፣ እንዲሞቱ አርጋችሁ፣
አስራ ሰባት ዓመት፣ ሀገር አቃጥላችሁ፣
አንድ ወጣት ትውልድ፣ መትራችሁ፣ አርዳችሁ፣
ዜጎችን አፍሳችሁ፣ በእሥር አፍናችሁ፣
በጭካኔ ጅራፍ፣ ግርፍ አሰቃይታችሁ፣
ለተረሸኑበት ዋጋ  አስከፍላችሁ፣
እናት ለልጇ ሞት፣ «እልል» አስብላችሁ፣
ወገን አስክሬን ላይ፣ እንዳልዘፈናችሁ?!

ዛሬም እንደትላንት፣ መግደል ናፈቃችሁ?!
የሠማዕታትን ገድል፣ በብለት ሸፍናችሁ?!
ደም በተነከረው፣  ጎልዳፋው ብዕራችሁ!
ታሪክ አጣማችሁ፣ ፃፍን ትላላችሁ?!

ምነው ቢበቃችሁ፣ አትርሱን ካላችሁ፣
እሺ እናስታውሳችሁ!
በያላችሁበት፣ እንደየሥራችሁ!
ፍርድ እስኪገኝ ድረስ፣ እስከነ ብጤያችሁ!
ዛሬም እንደትላንት፣ መግደል ናፈቃችሁ!?

የምን አትርሱን ነው፣ እኛስ መች ስንረሳ?!
ሀቅ አይለቃችሁም፣ ካላገኘ በቀር፣ ፍትህ የደም ካሳ!!!

አፕሪል 19 ቀን 2014